# የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የተጠቃሚዎች ልየታ መመሪያ

## ቁጥር 04/2009

**ታህሳስ 20 2009 ዓ.ም**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

## መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ድህነትና ኋላቀርነትን ለማስወገድና ወደ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ ራዕይ ሰንቃ ጉዞ ከጀመረች ዓመታት አስቆጥራለች፡፡ በነዚህም አመታት በርካታ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን አመርቂ ውጤትም ተመዝግቧል፡፡ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻርም መንግስት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ሳይረጋገጥና የተሟላ ተሳትፎና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት እውን ሳይሆን ወደ ታሰበው ራዕይ ለመድረስ አዳጋች መሆኑን በመገንዘብ የገጠር ሴፍቲኔት ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ዜጎች ከምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነት እንዲላቀቁና የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻል አድርጓል፡፡

የከተማችን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በዋናነኝነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በተለይም በከተማችን የሚታዩ በድህነት ውስጥ የሚገኙ እና ለተለያዩ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል፡፡በመሆኑም ወደ ትግበራ ምዕራፍ ለመግባት ከሚሰሩት ዋነኛ ስራዎች መካከል ተጠቃሚዎችን በቤተሰብ ደረጃ የልየታ ስራ አንዱ ሲሆን የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን ከኪራይ ሰብሳቢነት በጸዳ እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ባሰፈነ መልኩ ለመለየት የተጠቃሚዎች ልየታ ስርዓት፣ የልየታ ሂደቶች፣መምረጫ መስፈርቶች፣ የምዝገባ ስርዓት ግልጽ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ የተጠቃሚዎች መመልመያ መስፈርት ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፡-

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀፅ 13 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የተጠቃሚዎች ልየታ መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ ‹‹**የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የተጠቃሚዎች ልየታ መመሪያ ቁጥር** 04/2009 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1) **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2) **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3) **'"ቢሮ"** ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ነው፤
4) **'"ኤጀንሲ"** ማለት የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፣
5) **"የምግብ ዋስትና"** ማለት መጠን እና ጥራትን በአማከለ መልኩ በዘላቂነት ምግብ በማግኘት የእያንዳንዱ ግለሰብ የነፍስ ወከፍ የዕለት ፍጆታን እስከ 2,200 ካሎሪ እንዲደርስ በማድረግ ጤናማና የተመጣጠነ የምግብ ዋስትና ኖሮት ጤነኛና አምራች ዜጋ እንዲሆን ማድረግ ነው፤
6) **"ልማታዊ ሴፍቲኔት"**፤- ማለት ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከልማት ስራ እና ከዘላቂ ሀብት ፈጠራ ስራዎች ጋር በማስተሳሰር የገቢ ምንጭ የማስገኛ አማራጮችን በማስፋትና ምርታማ እንዲሆኑ በማብቃት የራሳቸውን ጥሪት ገንብተው የምግብ ዋስትናቸውን በዘላቂነት እንዲያረጋግጡ ማስቻል ነው፡፡
7) **"የሥራ ዕድል"**፡-ማለት የመሥራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ ያልገቡ ነዋሪዎች በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ገቢ የሚያገኙበት የድጋፍ ዓይነት ነው፡፡
8) **"ልየታ"**፡-ማለት በከተማው የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በቀጥታ ድጋፍ እና በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ንዑስ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የሚሆኑ ግለሰቦች እና ቤተሰቦችን የመምረጥ ሂደት ነው፤
9) **"የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ"** ማለት በምግብ ዋስትና ፕሮግራም በቤተሰብ ደረጃ ከተለየ በኋላ በቀጥታ ድጋፍ ፣ በአካባቢ ልማት ስራዎች እና በኑሮማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች የሚታቀፍ ቤተሰብ ነው፡፡
10) **"ህጋዊ ማስረጃ"** ማለት ዕድሜን፣ ነዋሪነትን፣ የአካል ጉዳትን፣ ህመምን፣ ሞትን እንዲሁም የመስራት ብቃትን አስመልክቶ ከሚመለከተው አካል የሚሰጥ 6 ወር ያላለፈው ማስረጃ ነው፤
11) **"የቀጥታ ድጋፍ"** ማለት በተደራራቢ የአካል ጉዳት እና በእድሜ ምክንያት ሰርተው ገቢ ለማግኘት የማይችሉ በቤተሰብ ደረጃ ከተለየ በኋላ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሚሆኑ በቀጥታ በገንዘብ ወይም በዓይነት ድጋፍ የሚሰጥበት የድጋፍ ዓይነት ነው፡፡

12) **"የማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች "**ማለት የአካባቢው አስተዳደርና በህብረተሰቡ የሚታቀዱ የአረንጓዴ ልማት፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ የወንዞች ዳርቻ ልማት፣ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ወዘተ ስራዎችን በመስራት የዕለት ገቢ ለማግኘት የሚያስችል የድጋፍ ዓይነት ነው፤

13) **"የኑሮ ማሻሻያ"** ማለት በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ በራሳቸው ጥረት አኗኗራቸውን ለማሻሻል የሚደረግ ጥረትን የሚደግፍ የድጋፍ ዓይነት ነው፤

14) **"የልየታ ኮሚቴ"** ማለት ከተለያዩ የማህበረሰብ አደረጃጀቶች ማለትም ከቀጠና ልማት ኮሚቴ፤ከወጣቶች፣ ከሴቶች፤የአከባቢ ሽማግሌ፤ከአረጋውያን ማህበር፤ ከአካል ጉዳተኞች ማህበር፤የአካባቢ ጤና ኤክስቴንሽን ፤ከወረዳው ሶሻል ወርከር እና ከእድሮች የሚወከሉ አባላት ያሉት ሆኖ በየቀጠናው የምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎችን ልየታ የሚያከናውን ኮሚቴ ነው፡፡

15) " **የቀጠና ልማት ኮሚቴ**" ማለት በመኖሪያ አካባቢ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጠና ልማት ላይ የሚመክር የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን የሚያስተባብር በኗሪው የሚመረጥ የኮሚቴ አደረጃጀት ነው፡፡

16) **"ሽግግር"** ፡-ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ ከማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች ወደ ኑሮ ማሻሻያ ከኑሮ ማሻሻያ ወደ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ማሸጋገር ነው ፡፡

17)**"ምርቃት"** ፡-ማለት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ከማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና ከዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ንዑሳን ፕሮግራም ተጠቃሚነት መውጣትን ያመለክታል፡፡

18) **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት ከስራው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው እና ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የመንግስት አካላት፣ የልማት አጋሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፤

19)**"ሰው "** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

20) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በቀጥታ ድጋፍ፣ በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች እና በኑሮ ማሻሻያ ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች መመልመያነት የሚያገለግል ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ዓላማ፤መርሆዎች፤አደረጃጀት፤ተግባርና ሃላፊነት እና የተጠቃሚዎች ልየታ ሂደት

4. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

በከተማችን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉትን ቤተሰቦች ተጠቃሚ ለማድረግ በአከባቢ ልማት ስራዎች እና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ አማካኝነት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ እና ከድህነት እንዲወጡ የሚያስችል የልየታ ስርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡

5. <u>የተጠቃሚዎች የልየታ መርሆዎች</u>

1. የጠባቂነት አመለካከትን መቅረፍ፣
2. የማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦችን በፍትሀዊነት የመጠቀም መብት ማረጋገጥ፣
3. ግልጽነትና ተጠያቂነት፣
4. የህብረተሰብ ተሳትፎን ማጠናከርና ከሌሎች የልማት ስራዎች ጋር ማስተሳሰር፣
5. ተከታታይነት ያለው መማማር፣
6. ሃብትን በተገቢው መንገድ መጠቀም፣
7. የተጠቃሚዎችና የባለድርሻ አካላትን መረጃ የማግኘትን መብት ማክበር፣
8. ምስጢር መጠበቅ፣

6. <u>የቀጠና የልየታ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>

የልየታ ኮሚቴ አደረጃጀት 9 አባላት ያሉት ሆኖ ተጠሪነቱም ለወረዳው የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ሲሆን እነሱም፡-

1) ከቀጠና ልማት ኮሚቴ(ሁለት)
2) የወረዳ ሶሻል ወርከር ባለሙያ
3) የቀጣና የሴቶች ልማት ቡድን ሰብሳቢ
4) የቀጠና የወጣቶች ልማት ቡድን ሰብሳቢ
5) ከአረጋውያን ማህበር ሰብሳቢ
6) ከአካል ጉዳተኞች ማህበር ሰብሳቢ
7) የአካባቢ ጤና ኤክስቴንሽን ተወካይ
8) የአከባቢ እድር ሰብሳቢ
9) የቀጠና ልየታ ኮሚቴ አደረጃጀት ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ቀጠናዎች የሚቋቋም ይሆናል፡፡

10) የቀጠና የልየታ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ም/ሰብሳቢ እና ጸሀፊ የሚሆኑትን በኮሚቴው አባላት የሚመረጡ ሲሆን የተወከሉትን ለወረዳው የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የሚያሳውቁ ይሆናል፤

## 7. የቀጠና የልየታ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1) የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን በመለየት የቤት ለቤት ምዝገባ በቀጠና ደረጃ ያከናዉናል፣
2) የተሰበሰበውን የተጠቃሚዎች መረጃ ተገቢ መሆኑን የማጣራት ስራ ያከናውናል፣
3) በተሰበሰበው መረጃ ላይ በመመስረት የተጠቃሚዎቹን ተገቢነት በተመለከተ በአካባቢው ማህበረሰብ በማስተቸት በተሰጠው ግብዓት መሠረት ማስተካከያ ያደርጋል፣
4) የልየታ አሰራሩን ውጤታማ ለማድረግ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣
5) ለቀጥታ ድጋፍ እና የማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች ንዑስ ፕሮግራም የተጠቃሚዎችን ዝርዝር እና ተጠቃሚዎቹ የሚሰማሩባቸውን የስራ ዓይነት በመለየት ለወረዳው የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት ያስተላልፋሉ፡፡
6) የወረዳው የቀጥታ ድጋፍ እና የማህበረሰብ አቀፍ ስራ የቴክኒክ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

## 8. የተጠቃሚዎች ልየታ ሂደት

1) በክፍለ ከተማ እና ወረዳ ያለውን ጠቅላላ የህዝብ ብዛት፣ ከድህነት ወልል በታች የሚኖረውን የህዝብ መጠን፣ በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች የሚለሙ ቦታዎችን እና ለስራ እድል ፈጠራ የሚሆኑ አካባቢያዊ ጸጋዎችን፣ በመለየት አጠቃላይ መረጃዎች ይያዛሉ፣
2) ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚደረግባቸው አካባቢዎች ተጠቃሚዎችን የሚለዩ የልየታ ኮሚቴ አባላት ስለልየታው አሰራርና አፈጻጸም በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡
3) ፕሮግራሙን ለመተግበር በተመረጡ ክፍለ ከተማና ወረዳ ያሉ የደሃ ደሃ የሆኑ ተጠቃሚዎችን በቤተሰብ ደረጃ በመለየት፣በመመዝገብ መረጃ በመያዝና የተጠቃሚዎችን ብዛት ለመወሰን ኃላፊነት ለተሰጠው አካል ይተላለፋል፣
4) ከስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ባለሙያዎች እና ከሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ባለሙያዎች በጋራ በመሆን ከልየታ ኮሚቴ የመጣላቸውን የተጠቃሚዎች ዝርዝር በመቀበል የቀረበለትን የተጠቃሚዎች ዝርዝር በድህነት መጠን መሰረት በደረጃ በማስቀመጥ፣ በየትኛው ፕሮግራም ዓይነት ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው በመለየት ለወረዳ ንዑስ ፕሮግራሙ ለሚመለከተው ቴክኒክ አስተባባሪ ኮሚቴ ያስተላልፋል፣
5) የወረዳው ቴክኒክ አስተባባሪ ኮሚቴ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጠቃሚዎችን ወስኖ ከማሳወቁ በፊት በአግባቡ ስለመመረጣቸው በኑሮ ደረጃ ምዘና እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

6) የወረዳው የስራ አመራር አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠንቶ በቀረበለት መረጃ መሰረት የመጨረሻ ተጠቃሚዎችን በመወሰን ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ በመለጠፍ እንዲታወቅ ያደርጋል፣
7) በተጠቃሚዎች ልየታ ላይ የሚነሳ ቅሬታ ካለ በቅሬታ ማስተናገጃ መመሪያ መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡
8) የተመረጡትን ተጠቃሚዎች ዝርዝር ወደ ዳታ ቤዝ በማስገባት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማስተላለፍ፣
9) የተመረጡ ተጠቃሚዎች በየንዑስ ፕሮግራሙ ስራ ውስጥ መግባታቸውንና ተጠቃሚ መሆን መጀመራቸውን ማረጋገጥ፡፡

# ክፍል ሶስት

# የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች፣ የልየታ ዘዴ፤መስፈርትና የመረጃ ሥርዓት

## 9. <u>የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች</u>

በከተማችን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡ ከእነዚህም የህብረተሰብ ክፍሎች፡-

1) ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ፣
2) ጎዳና ተዳዳሪዎች፤
3) ለምኖ አዳሪዎች፣
4) ሴተኛ አዳሪዎች፣
5) ስራ አጥ ዜጎች፣
6) አካል ጉዳተኞች፤
7) የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች፣
8) አረጋውያን፤

## 10. <u>የተጠቃሚዎች ልየታ ዘዴዎች</u>

1) የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በዋነኝነት ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ በተለይም ለተለያዩ ለኢኮኖሚያዊ እና ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡
2) የተጠቃሚዎች ልየታ ስርዓት ከገጠር የልማታዊ ሴፍቲኔት ምልመላ ስርዓት ጋር ቁርኝት ያለው እና የከተማችንን ልዩ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ በዋነኝነት፡-
   ሀ) በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ
   ለ) በማህበረሰብ ተሳትፎ

ሐ) የቡድን

መ) የኑሮ ደረጃ ምዘና

ሠ) እራስን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለፕሮግራሙ እጩ በማድረግ

ረ) ከላይ ከተመለከቱት ሊጣጣሙ ከሚችሉ ሁለትና ከዚያ በላይ መመዘኛዎችን በጣምራ በመጠቀም የተጠቃሚዎች ምልመላ የሚከናወን ይሆናል፡

11.<u>የተጠቃሚዎች የልየታ መስፈርት፤</u>

የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት የልየታ መስፍርቶች ይኖሩታል፣

1. <u>የወረዳ ልየታ መስፈርቶች ከመቶኛ፤</u>

ሀ) የወረዳው የድህነት ወለል(25)፣

ለ) በወረዳው የሚኖሩ የህዝብ ቁጥር (20)፣

ሐ) የወረዳው የስራ አጥነት ምጣኔ (20)፣

መ) በወረዳው የማህበራዊ ኑሮ ችግር እና የአደጋ ተጋላጮች ብዛት (10)፣

ሠ) የወረዳው የዕድገት ደረጃ፣(10)፣

ረ) በወረዳው የገጠር ነዋሪ የፍልሰት መጠን(5)፣

ሰ) ወረዳው ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ዝግጁነት(10)

ቀ) የከተማው ኤጀንሲ ወረዳዎችን በድህነት መጠናቸው የመለየት ስራ ይሰራል፤ ከእያንዳንዱ ወረዳ የሚመረጡ ተጠቃሚዎችን መወሰን፣የተመረጡትን ተጠቃሚዎች ለህብረተሰቡ ማሳወቅና በልየታ ሂደትም ቅሬታ ካለ የማስተናገድ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

2. <u>የቀጠና ልየታ መስፈርቶች ከመቶኛ፤</u>

ሀ) ከድህነት ወለል በታች ያሉ ቤተሰቦች ብዛት(25)፣

ለ) የስራ አጦች ብዛት(20)፣

ሐ) የማህበራዊ ኑሮ ችግር ተጋላጮች ብዛት (15)፣

መ) ለኢ-መደበኛ ስራዎች ተጋላጭ የሆኑ ሰፈሮች (10)፣

ሠ) ለሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች የተጋለጡ ሰፈሮች(10)፣

ረ) ሌሎች የልማት ፕሮግራሞች በብዛት የማይገኙባቸው ሰፈሮች(8)፣

ሰ) የመሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ሽፋን(6)፣

ሸ) ሰፈር ውስጥ ያሉ የመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ(6)፣

ቀ) የተጠመረጡትን ተጠቃሚዎች ለህብረተሰቡ ማሳወቅና በልየታ ሂደትም ቅሬታ ካለ የማስተናገድ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

3.<u>የቤተሰብ ልየታ መስፈርቶች</u>

ሀ) አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢው በቀን ከ 2 ዶላር በታች የሆነ መሆኑ፣

ለ) ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ቀጠና ለ6 ወር እና ከዚያ በላይ መኖሩ የተረጋገጠ ወይም ሲኖርበት ከነበረ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ መሸኛ ማምጣት ከቻለ፣

ሐ) በፕሮግራሙ ለመሳተፍ የሚያበቃዉን መስፈርት ማሟላቱን በልየታ ኮሚቴ ተመልምሎ የሚገባዉ መሆኑን በአካባቢዉ ማህበረሰብ የተረጋገጠ ከሆነ፣

መ) በሌሎች የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት እና የእርዳታ ፕሮግራሞች ያልታቀፉ ቤተሰቦች፣

4. <u>የቀጥታ ድጋፍ ንኡስ ፕሮግራም የተጠቀሚዎች መመልመያ መስፈርቶች</u>

ሀ) ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን እና ወላጅ አልባና ደጋፊ የሌላቸው ሕጻናት፣

ለ) በህመም ምክንያት ራሳቸውንም ሆነ ልጆቻቸውን ሰርተው ማስተዳደር የማይችሉ ቤተሰቦች፣

ሐ) በተደራራቢ አካል ጉዳት ምክንያት መስራት የማይችሉ እና ደጋፊ የሌላቸው አካል ጉዳተኞች፣

መ) የሚደግፉቸው ቤተሰብ የሌላቸው በኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ ምክንያት የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ዜጎች፣

ሠ) በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች በራሳቸው ወይም በሚወክሉት ሰው አማካኝነት የባንክ ሂሳብ ተከፍቶ በየወሩ ብር 170 ገቢ ይደረግላቸዋል፡፡

5. <u>በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች የሚሳተፉትን ቤተሰቦች የልየታ መስፈርቶች፣</u>

ሀ) ከድህነት ወለል በታች ሆነዉ የመሥራት አቅም ያላቸው፣

ለ) ከድህነት ወለል በታች የሆኑ ስራ አጦች መሆናቸው የተረጋገጠ፣

ሐ) ከ18 ዓመት በላይ የሆነው የቤተሰቡ አባልና በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆነ፣

መ) ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ እስከ አራት የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣

ሠ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሆነው ወልደው የሚያጠቡ እናቶችና ነፍሰ ጡር ሴቶች ሊተካቸው የሚችል የቤተሰብ አባል ካለ ሊተኩ ይችላሉ፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 ከተራ ፊድል ሀ እስከ ሠ በተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚታቀፉ ተጠቃሚዎች የቀን የጉልበት ክፍያ 60 ብር ሆኖ በቀጣይ በአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከሚያገኙት ዕለታዊ ገቢ 80 በመቶው ለፍጆታ የሚያውሉት ሲሆን 20 በመቶውን እንዲቆጥቡ በማድረግ ከፕሮግራሙ 40 በመቶ ተጨማሪ ድጋፍ በቁጠባቸው በባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡

ሰ) በአካባቢ ልማት የሚሳተፉ ቤተሰቦች በመጀመሪው አመት 240 ቀናት በሁለተኛው አመት 160 ቀናት እና በሶስተኛው አመት 80 ቀናት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

6. <u>በኑሮ ማሻሻያ የሚሳተፉ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የልየታ መስፈርቶች፣</u>

ሀ) በማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች ተሰማርተው አስፈላጊው የቁጠባ መጠን ያላቸው፣

ለ) ከቤተሰቡ አባል አንዱ ስልጠና ለመውሰድ ዝግጁ የሆነና አዋጭ ቢዝነስ ፕላን ማቅረብ የሚችል፣

ሐ) በኢ-መደበኛ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙና ወደ ህጋዊ አሰራር ለመግባት ፍቃደኛ የሆኑ፣

መ) መንግስት የሚያመቻቸውን ድጋፍ በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ዝግጁ የሆነ፣

ሠ) መንግስት የሚፈጥርለትን የስራ ትስስር በአግባቡ ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ፣

ረ) የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ ኢንተርፕራይዝ ለመመስረት ዝግጁ የሆነ፤

ሰ) በዚህ ንኡስ ፕሮግራም ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች በባንክ ሂሳባቸው ብር 10,000 (አስር ሺ ብር) ለስራ ማስጀመሪያ የሚሆን መነሻ ካፒታል ገቢ ይደረግላቸዋል፡፡

12. <u>የተጠቃሚዎች ልየታ የመረጃ ስርዓት</u>

1) በፕሮግራሙ ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ከሚኖራቸው ጉዳዮች አንዱ የመረጃ ስርዓቱ በመሆኑ የሁለቱም ንዑስ ፕሮግራሞች መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የታገዘ እንዲሆን ይደረጋል፣

2) የመረጃ ስርዓቱ የተጠቃሚውን ጥሬ ሀቅና የቀረበለትን ድጋፍ ዓይነት በዝርዝር የሚያሳይ ይሆናል፡፡ በመረጃ ስርዓቱ እንዲካተቱ የሚፈለጉ ዋና ዋና ጉዳዮችም የተጠቃሚዎች ስም፣ ዕድሜ፣ መለያ ኮድ፣ የቤተሰብ አባላት ብዛት፤ የሚገኙበት ክፍለ ከተማ፣ ወረዳና ቀጠና፣ የሚሳተፉበት ንዑስ ፕሮግራም አይነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኑሮ ሁኔታ አመታዊ ወይም የዕለት ገቢ፣ ስራ ውስጥ ያለ ከሆነ የስራ ሁኔታ፣የሚያገኙት የድጋፍ አይነት እንዲሁም የቆይታ ጊዜን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎች በመረጃ ስርዓቱ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

3) የተጠቃሚዎች መረጃ በስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ተቋሞች የሚሰበሰቡና የሚደራጁ ይሆናል፡፡

13) <u>የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ ዘዴዎች</u>

በተለያዩ ዜዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ወደ መረጃ ስርዓቱ ከመግባቱ በፊት በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ለሚመለከታቸው ተቋማት በመድረክ ውይይት ወይም በማስታወቂያ ቦርድ በመለጠፍ ቀርቦ እንዲተች በማድረግ የተጠቃሚዎችን መረጃ ጥራት የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡

# ክፍል አራት

## የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

14) **<u>የኤጀንሲዉ ተግባር እና ኃላፊነት፡-</u>**

ሀ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች የልየታ መመሪያ ያዘጋጃል፣

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ልየታ ዙሪያ በተዋረድ ላሉ አደረጃጀቶች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣

ሐ) በየደረጃው ተጠቃሚ ቤተሰቦች በመመሪያው መሰረት መለየታቸውንና መመዝገባቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

መ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፉ ያደርጋል፣

ሠ) የተጠቃሚዎችን መረጃ በአግባቡ ይሰበስባል፣ ያደራጃል በወቅቱ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ ያደርጋል፣

ረ) በየደረጃው ለቀረቡ ቅሬታዎች መፍትሄና ግብረ መልስ ይሰጣል፣

ሰ) በአፈጻጸም ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን እና ጠንካራ ጎኖችን በጋራ ይገመግማል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

ሸ) አፈጻጸሙን ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

15.**<u>የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ</u>**

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች መመልመያ መመሪያ ዝግጅት ላይ የጋራ ተሳትፎ ያደርጋል፣

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች ምልመላ ዙሪያ የጋራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለምልመላ ስራ አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣

ሐ) ለጎዳና ነዋሪዎች፣ ለሴተኛ አዳሪዎችና ለለምኖ አዳሪዎች የስነ ልቦና ትምህርት በመስጠት በምግብ ዋስትና ፕሮግራም እንዲታቀፉ በጋራ ይሰራል፣

መ) በቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሠ) የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ቤተሰቦች መረጃ በተዋረድ ባሉ ጽ/ቤቶች በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፣

ረ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች ቅሬታና አቤቱታ መፈታቱን ይከታተላል፣ የመፍትሄ አቅጣጫም ይሰጣል፣

ሰ) የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን ምልመላ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፉ ያደርጋል፣

ሸ) አፈጻጸሙን ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

16. **የክፍለ ከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት እና ባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት፡-**

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች የልየታ መስፈርቶች ዙሪያ በጋራ ግብአት ይሰጣል፣

ለ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች የልየታ መመሪያ ላይ ለወረዳዎች እና ለቀጠናዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣

ሐ) በየደረጃው ተጠቃሚ ቤተሰቦች በመመሪያው መሰረት መለየታቸዉና መመዝገባቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

መ) የተጠቃሚ ቤተሰቦች መረጃን በአግባቡ ይሰበስባል፣ ያደራጃል እንዲሁም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፣

ሠ) በየደረጃው ለቀረቡ ቅሬታና አቤቱታዎች መፍትሄ ይሰጣል፣

ረ) በአፈጻጸም ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን እና ጠንካራ ጎኖችን በጋራ ይገመግማል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

ሰ) አፈጻጸሙን ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ያደርጋሉ፣

17) **የወረዳ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት እና የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት፡-**

ሀ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች የልየታ መስፈርት ላይ በጋራ አስተያየት ይሰጣሉ፣

ለ) የቀጠና ልየታ ኮሚቴ በጋራ ያደራጃሉ፣

ሐ) ስለ ልየታ መመሪያና አፈጻጸም ለቀጠና ኮሚቴና ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣

መ) በኮሚቴው አማካኝነት ተጠቃሚ ቤተሰቦች እንዲለዩና እንዲመዘገቡ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፣

ሠ) የተጠቃሚ ቤተሰቦችን መረጃ በአግባቡ ይይዛል፣ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋሉ፣

ረ) ለተጠቃሚ ቤተሰቦች ቅሬታ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋሉ፣

ሰ) በተጠቃሚ ቤተሰቦች የልየታ አፈጻጸም ዙሪያ የጋራ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፣

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18) <u>የመተባበር ግዴታ</u>

አስፈጻሚ አካላት፣የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች፣ የሚመለከታቸው ተቋማት እና የተለያዩ የህዝብ አደረጃጀቶች ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

19) <u>የተጠቃሚ ቤተሰቦች ልየታ የሚከናወንበት ጊዜ</u>

የተጠቃሚዎች ምዝገባ በዓመት አንድ ጊዜ በጣት አሻራ እና በፎቶ ግራፍ በማስደገፍ በ1ኛው ሩብ ዓመት የሚከናወን ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በማንኛውም ጊዜ የሚከለስ ይሆናል፡፡ ለተጠቃሚ ቤተሰቦችም የመለያ ቁጥርና መታወቂያ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡ ምዝገባውም በከተማ ደረጃ ፕሮግራሙ በሚጀመርባቸው ወረዳዎችና ቀጠናዎች በተመሳሳይ ወቅት የሚከናወን ይሆናል፡፡

20) <u>ተጠያቂነት</u>

1. ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፣
2. ኃላፊነትን የማይወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፣

21) <u>መመሪያውን ስለ ማሻሻል</u>

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

22) <u>ተቀባይነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

23) <u>መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በቢሮው ፀድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**አቶ ልዑልሰገድ ይፍሩ**

**የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ**